# ተሽከርካሪዎች በልዩ መብት በቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ ወደ

# ሀገር ስለሚገቡበት ሁኔታ የተሰጠው መብት ስለመሻሻሉ

# የወጣ መመሪያ ቁጥር 36/98

የጉምሩክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ታሪፍ ደንብ ቁጥር 122/85 ሁለተኛ መደብ አንቀጽ /ለ/ ንዑስ አንቀፅ 2/ለ/ ለማሻሻል በወጣው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 6/88 አንቀጽ 2 መሠረት በውጭ አገር በኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን አገልግለው ወይም ለሌላ የመንግስት ሥራ ለትምህርት ለግል ሥራ በስደት ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ውጭ ቆይተው የሚመለሱ ወይም መንግሥት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሠረት የሚወጡ ኢትዮጵያን፣ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን እንዲሁም አካል ጉዳተኞች እና ተሸላሚ ኢትዮጵዊያን የፌደራል መንግሥት የገቢዎች ሚኒስቴር በአወጣቸው መመሪያዎች መሠረት የግል መገልገያ እና በሽልማት የተገኙ እቃዎቻቸውን ወደ ሀገር ውስጥ በቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ እንዲያስገቡ ሲደረግ ቆይታል።

በተጠቀሱት መመሪያዎች ተሽከርካሪን በተመለከተ የተሰጡ መብቶችን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/95 አንቀፅ 3 እና በደንብ ቁጥር 6/88 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ ለ/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ በልዩ መብት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 36/98 ተብሎ ሊጠ ቀስ ይችላል።

2. **ማሻሻያ**

2.1 በልዩ መብት ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥ እና ታክስ ክፍያ የግል መገልገያ እቃዎች ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጡት የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያዎች ቁጥር 7/1996፣ 22/1997 እና 29/1998 እንደሚከተለው ተሻሽለዋል።

በመመሪያዎቹ:

- በኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚስዮን አገልግለው ለሚመለሱ፣
- በተለያዩ የኢዮጵያ መንግሥት ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች አገልግለው ለሚመለሱ፣
- ለኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ባህርተኞች፣
- በአሕጉራዊና ዓለም አቀፉዊ ድርጅቶች ውስጥ ሲያገለግሉ ቆይተው ለሚመለሱ ኢትዮጵያውያን፣

- በትምህርት ውጭ ቆይተው ለሚመለሱ፣
- በስደት ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ ቆይተው ጠቅልለው ለሚመለሱ ኢትዮጵያዊያን፣
- ለአካል ጉዳተኞች፣
- መንግሥት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ ለሚመጡ ባለሙያዎች እና
- የቅጥርና የሥራ ውል አድርገው ለሚመጡ ባለሙያዎች ተሰጥቶ የነበረው፣ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ የግል ተሽከርካሪን የማስገባት ፈቃድ በዚህ መመሪያ ተነስቷል፡፡

2.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2.1 የተደነገገው ቢኖርም

- በኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን፣
- በተለያዩ የኢትዮጵያ መንግስት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች፣
- የኢትዩጵያ ንግድ መርከብ ባህርተኞችና
- በአሕጉራዊና አለም አቀፋዊ ድርጅቶች ውስጥ ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ ሲያገለግለ ቆይተው የሚመለሱ ኢትዮጵያዊያን አንድ የግል አውቶሞቢል ቀረጥና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ፡፡

2.3 በተመሳሳይ ሁኔታም በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ቆይተው ጠቅልለው ወደአገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን አንድ የግል አውቶሞቢል ቀረጥና ታክስ

በመክፈል ማስገባት ይችላሉ፡፡

የሽልማት እቃዎችን ወደ አገር ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣው የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 23/1997 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሠርዞ ማንኛውም ሰው በውጭ አገር በታወቁ የዓለምና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች አገርንና ሕዝብን ወክሎ ወይም በግል በውድድር መካፈል ባገኘው የብልጫ ውጤት መሠረት ከተሽከርካሪ በስተቀር ማናቸውንም የሽልማት እቃዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ክፍያ በነፃ ወደ ሀገር ያስገባል፡፡ በሽልማት የተገኘው ተሽከርካሪ ከሆነ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገባል፡፡ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገባ፣ ለሁለተኛ እና ከዚያ በላይ ተሽከርካሪያን በሽልማት ካገኘ በቀረጥና ታክስ ክፍያ ያስገባል በሚል ተስተካክላል፡፡

2.4 ለአካል ጉዳተኞች የሚያገለግሉ ልዩ እቃዎችና መሣሪያዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ስለሚገቡበት ሁኔታ ግንቦት 15 ቀን 1994 ዓ.ም. በቁጥር 01/ገ2/64//6 የወጣው መመሪያ እንደሚከተለው ተሻሽላል፡፡

2.5.1 በመመሪያው በተለያዩ አንቀጾች "አካለስንኩል" በሚል የተገለጸው የአካል ጉዳተኛ በሚል ተስተካክሏል፡፡

2.5.2 የመመሪያው አንቀጽ 3 ተሠርዞ ከዚህ በሚከተለው ተተክቷል፡፡ ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ ለተጐዳው አካሉ ቀጥተኛ ድጋፍ የሚሰጡ ከመኪና በስተቀር ልዩ እቃዎችንና መሣሪያዎችን ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

3. <u>መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ</u>

3.1 ይህ መመሪያ ከሐምሌ 17/1998 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

3.2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ከፀናበት ዕለት አስቀድሞ ወደ ሀገር ለመግባት በተጫኑ፣ በመጓጓዝ ላይ በሚገኙና ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም በቀረቡ የግል አውቶሞቢሎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

# የገቢዎች ሚኒስቴር

## መመሪያ ቁጥር 7/1996

## በልዩ መብት ከቀረጥና ታክስ ነጻ እና ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ የግል መገልገያ እቃዎች ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ጓዛቸውን ጠቅልለው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያ ተወላጅ የውጭ ዜጎች የሚያስገቧቸው የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች አግባብ ካለው የመንግሥት መ/ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙ የውጭ ባለሀብቶች እና በውጭ አገር በዘላቂነት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች እንዲሁም በኢትዮጵያ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ የውጭ ዜጎች/ሰዎች ለግል መገልገያ ሰለሚያስገቧቸው ዕቃዎች አፈጻጸም ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1995 አንቀጽ 3 መሠረት የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ እንደሚያወጣ የተደነገገ በመሆኑ፣

የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 122/85ን ለማሻሻል በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 6/88 አንቀጽ 2 መሰረት የጉምሩክ የዕቃ ቀረጥ ሥርዓትና ተመን ሁለተኛ መደብ አንቀጽ ለ(2) ለ (እንደተሻሻለው) በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ጓዛቸውን ጠቅለው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን እና በተራድኦ ስምምነት መሠረት የሚመጡ የውጭ ዜጎች ከቀረጥ ነጻ የሚያስገቧቸውን የግል መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር የፌዴራል መንግስት የገቢዎች ቦርድ እንደሚያወጣ የተደነገገ እና ይህም ለገቢዎች ሚኒስቴር የተላለፈ በመሆኑ፣

እስካሁን በሥራ ላይ ያለው መመሪያ በርካታ ጊዜያት ማሻሻል የተደረገበት በመሆኑ ለአጠቃቀም አመቺ ካለመሆኑም በላይ በአፈጻጸም ወቅት ለተከሰቱ በርካታ ችግሮች ለወደፊት መፍትሄ ለመስጠት እና ከዘመኑ የቴክኖሎጂና የአኗኗር ዕድገት አንጻር ነባሩን መመሪያ ማሻሻልና በአንድ ወጥ አዲስ መመሪያ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የገቢዎች ሚኒስቴር በደንቡ ቁጥር 88/95 አንቀጽ እና በደንብ ቁጥር 6/88 (እንደተሸሻለ) አንቀጽ ለ(2) ለ መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ</u>

***<u>አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ</u>***

*ይህ መመሪያ በልዩ መብት ከቀረጥና ታክስ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ የግል መገልገያ እቃዎች፤ ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 7/1996 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::*

***<u>አንቀጽ 2 ትርጓሜ</u>***

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. «ስደተኛ» ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ከአገሩ ወጥቶ በስደት የኖረና በራሱ ፈቃድ ወይም በመንግሥት ስምምነት ያለፓስፖርት ወደአገሩ የሚመለስ ወይም በተቀባይ አገር የጥገኝነት ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ እና በራሱ ፈቃድ በሊሴ ፓሴ ወይም በነበረበት አገር መንግስት ተገዶ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ነው::

2. «ተመላሽ» ማለት በሕጋዊ መንገድ ከኢትዮጵያ ወጥቶ በሄደበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቶ የኖረና ጠቅልሎ የሚመለስ ወይም ሕጋዊ ወይም ሕጋዊ ባልሆኑ የተለያዩ መንገዶች ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ የአገሩን ፓስፖርት እንደዚሁም ከኖረበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቶ የኖረና ጠቅልሎ የሚመለስ ነው:: የመኖሪያ ፈቃድ አሠራር በሌለበት አገር የኢትዮጵያን ፓስፖርት የያዙና እያሳደሱ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በዚህ ትርጉም የሚሸፈኑ ይሆናሉ::

3. «ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ» ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/94 መሠረት በወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት የኢትዮጵያ ተወላጅ የውጭ ዜጋ የመታወቂያ ካርድ የተሰጠው ሰው ሲሆን የመታወቂያ ካርዱ ጊዜውን ጠብቆ የታደሰለት እና ያልተሰረዘበት ነው::

4. «ዲፕሎማት» ማለት በኢትዮጵያ ሚሲዮን ወይም ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ በዲፕሎማትነት የተመደበ ወይም በኃለኞቹ ተቋማት ውስጥ ራሱ ተወዳድሮ የተቀጠረና የዲፕሎማቲክ ማዕረግ ያለው ወይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እውቅና ባገኙ ተቋማት ተመድቦ የሠራና የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ያለው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

5. «ቤተሰብ» ማለት የትዳር ጓደኛንና በእነርሱ ሥር የሚተዳደሩ ልጆቻቸውን የጨምራል፡፡

6. «የግል አውቶሞቢል» ማለት የመቀመጫ ወንበሩ በዛት ከ10 ያልበለጠ እና ለቤት አገልግሎት የሚውል ነው፡፡

7. «አንድ የትምህርት ዘመን» ማለት የከፍተኛ ትምህርት ለማጠናቀቅ የሚወስድ ጊዜ ሲሆን በማናቸውም ሁኔታ ከዘጠኝ ወራት የማያንስ ነው፡፡

8. «ባለሥልጣን» ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

9. «ቅርንጫፍ መ/ቤት» ማለት ዋናው መ/ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ የመንግስት መ/ቤት ወይም የመንግስት የልማት ደርጅት ወይም በመንግስትና በግል በጋራ የተቋቋመ ድርጅት በውጭ ያለ ቅርንጫፍ መ/ቤት ሲሆን የኢትዮጵያ ንግድ መርከብን የጨምራል፡፡

10. «ከፍተኛ ትምህርት» ማለት በትምህርት ሚኒሰቴር የከፍተኛ ትምህርት ካሪኩለም የሚታቀፍ ወይም የትምህርት ሚኒስቴር የሚቀበለው የመጀመሪያ ዲግሪና በላይ የሆነ ትምህርት ነው፡፡

11. «የግል መገልገያ» ማለት ከአንድ ግለሰብ አገልግሎት ጥቅም እና ይዞታ ጋር የተቆራኘ በህይወት ባለ ጊዜ አጭር ወይም ለረዥም ጊዜያት የሚጠቀምበት ተንቀሳቃሽ፤ ያገለገለ ወይም አዲስ ለንግድ የማይውል ዕቃ ነው፡፡

12.«የቤት ውስጥ መገልገያ» ማለት በአንድ ጣሪያ ስር ከሚኖር ቤተሰብ ጥቅም፤ አገልግሎት፤ ይዞታ እና ፍጆታ ጋር የተቆራኙ በቤተሰቡ ጥቅም ላይ የቆዩ ወይም የሚቆዩ ያገለገሉ እና አዳዲስ ከቤተሰቡ ውጪ ለሌሎች ሰዎች አገልግሎት እና ጥቅም እንዲውሉ ያልታቀዱ ወይም ለንግድ የማይውሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን የሚያካትቱ ዕቃዎች ናችው።

13. «የንግድ መጠን የሌለው ዕቃ» ማለት ከግል እና ከቤት ውስጥ መገልገያነት ውጪ በሽያጭ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ጠቅም ላይ በመዋል ትርፍ የማያስገኝ ዕቃ ነው።

**አንቀጽ 3 የመመሪያው ዓላማዎች**

**የመመሪያው ዋና ዋና ዓላማዎች:-**

1. በመንግስት ሥራ፤ በትምህርት፤ በግል ሥራ፤በስደት ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ባገኙት ሀብትና እውቀት ለአገራቸው እድገትና ልማት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማበረታታት፤
2. በዕድሜያቸው የገፉ ዜጎች የሽምግልና/ጡረታ ዕድሜያቸውን ከወገናቸው ጋር እንዲያሳልፉ ለማስቻል፤
3. ኢትዮጵያውያን በውጭ ያፈሩትን ሀብት ይዘው እንዲገቡ ለመርዳት ወይም ለመሳብ፤
4. ትውልድ ኢትዮጵያውያን የውጭ ዜጎች ከትውልድ አገራችው ጋር ያላቸው ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለመርዳትና ለአገሪቱ እድገትና ለወገኖቻቸው ኑሮ መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፤

5. በኢንቨስተርነት፤ በተራድኦ ስምምነት እና ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የሚመጡ የውጪ ዜጎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን የግል መገልገያ ዕቃዎች ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ፤ በቀረጥና ታክስ ነጻ እና ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ እንዲያስገቡ ለማስቻል ነው።

## አንቀጽ 4

## የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው የቅርንጫፍ መ/ቤት ወይም ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓላም አቀፍ ድርጅቶች ባልደረባ የሆኑ ኢትዮጵያውያን፤ በመንግስት ሥራ፤ በትምህርት፤ በግል ሥራ፤ በስደት፤ በሕክምና ወይም በጉብኝት ውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን፤ በመንግስት ጥሪ የሚመጡ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የውጭ ዜጎች ኢንቨስተር ሆነው የሚመጡትን ጨምሮ፤ የውጭ ኢንቨስተሮች፤ በተራድኦ ስምምነት የሚመጡ የውጭ ዜጎች በዚሁ መመሪያ መሠረት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ከቀረጥና ታክስ ነጻ እና ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ ወደ አገር በሚያስገቧቸው የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ላይ ነው፡፡

2. ከማዕድን ፍለጋና ማምረት ሥራ ጋር በተያያዘ የሚመጡ የውጭ ኢንቨስተሮች፤ አማካሪዎችና ተቋራጮች እንዲሁም ሠራተኞቻቸው የሚያስገቧቸው የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች በማዕድን አዋጅ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>አንቀጽ 5 የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን የማስገባት መብት</u>

1. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ሰዎች በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ሲያሟሉ እና ማስርጃዎችን ሲያቀርቡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 በተመደበው ምድብ መሠረት የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎቻቸውን ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ከቀረጥ ነጻና ቀረጥ ተከፍሎባቸው ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ድንጋጌ ቢኖርም ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ የግል መገልገያ ዕቃውን ከማስገባቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት የሚለይ ኢትዮጵያዊ ሕጋዊ ወራሾች እና ወይም ባል/ሚስት የሟቹን የግል መገልገያ እቃዎች ሟቹ ከነበረበት አገር በሟቹ ስም ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ከቀረጥና

ታክስ ነጻ እና ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ ሊያስገቡ የሚችሉ ሲሆን ሟቹ የግል መገልገያ እቃዎቹን ለማስገባት በሂደት ላይ እያለ ከሞተ ግን ሟቹ እቃዎቹን ለማምጣት ሂደት ከጀመረበት አገር ሁሉ ሊያስመጡ ይችላሉ፡፡

3. የሟቾቹ ወራሾች እና ወይም ባል/ሚስት በውጭ አገር ነዋሪ ከሆኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት ጠቅለው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 6 የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች አገባብ

1. በዚህ መመሪያ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን የማስገባት መብት የተፈቀደላቸው ኢትዮጵያውያን እና የውጭ ዜጎች እንደየምድባቸው የሚያስገቧቸው ዕቃዎች በዚህ እንቀጽ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡

2. ምድብ አንድ እና ሁለት

2.1 በዚህ ምድብ የተመደቡ ባለመብቶች ማንኛውንም የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ከቀረጥ ነጻ ማስገባት ይችላሉ፡፡

2.2 የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ የሆኑ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የሳሎን እና የመኝታ ቤት ዕቃዎች ከየእያንዳንዱ አንድ አንድ በቁጥር ወይም እንደ ዕቃው ባህሪ በሴት እንድ ከቀረጥ ነጻ ማስገባት ይችላሉ፡፡

2.3 ስላይድ ፕሮጀክተር እና አምስት ሰው የሚይዝ ጀልባ ቀረጥ እና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ፡፡

2.4 ከ29 ኢንች በላይ የሆን ቴሌቪዥን በልዩነቱ ላይ ቀረጥ እና ታክስ ተከፍሎበት ማስገባት ይችላል፡፡

## 3) ምድብ ሶስት

3.1 በዚህ ምድብ የተመደቡ ባለመብቶች ከዚህ በታች በቁጥር 3.3 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነጻ ማስገባት ይችላሉ፡፡

3.2 የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ የሆኑ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የሳሎን እና የመኝታ ቤት ዕቃዎች ከየአንዳንዱ አንድ አንድ በቁጥር ወይም እንደ ዕቃው ባህሪ በሴት አንድ ከቀረጥ ነጻ ማስገባት ይችላሉ፡፡

3.3 ኮንትሮል ቢፌ፤ የመጽሐፍ መደርደሪያ ሼልፍ፤ የአየር ማስወጫ እና ሽታ መከላከያ፤ኤር ኮንዲሽነር/መናፈሻ ወንበር አልጋ፤ ድንኳን፤ የመጸዳጃ ገንዳ የሳር ማጨጃ መኪና፤ ጀኔሬቱር ባለ 4 ኪሎ፤ የመኪና ጎማ የመኪና ጎማ ከነቸርኬው፤ ሃንድ ቱል ሴት አነስተኛ፤ ስላድ ፕሮጀክተር እና 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ ቀረጥ እና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ፡፡

## 4. ምድብ አራት

4.1 በዚህ ምድብ የተመደቡ ባለመብቶች ከዚህ በታች በቁጥር 4.3 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም የግል የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላሉ፡፡

4.2 ከዚህ በታች በቁጥር 4.3 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ የሆኑ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የሳሎን እና የመኝታ ቤት ዕቃዎች ከየአንዳንዱ አንድ አንድ በቁጥር ወይም እንደ ዕቃው ባህሪ በሴት አንድ ከቀረጥ ነጻ ማስገባት ይችላሉ፡፡

4.3 ቁም ሳጥን፤ አረቢያን መጅሊስ፤ ሶፋ፤ የመጠጥ/የዕቃ ማመላለሻ ጋሪ፤ የጋዝ ምድጃ፤ የጋዝ ስሊንደር ትልቁ፤ የውሃ ማሞቂያ፤ የባኞ ገንዳ፤ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስክሌት/መሮጫ/፤ የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻ ሴት፤ ፒያኖ ለቤት ውስጥ አገልግሎት፤ ጊታር፤ቪዲዮ ካሜራ፤ የዕቃ ማጠቢያ ማሽን፤ የሳር ማጨጃ መኪና፤ ጀኔሬተር ባለ 4 ኪሎ፤ ሀንድ ቱል ሴት

አነስተኛ፤ ሳተላይት ዲሽ ከነሪሲቨሩ፤ የልብስ ስፌት መኪና ከነዲናሞው፤ የመኪና ጎማ ከነቻርኬው፤ ኮነትሮል ብሬ፤ የመጽሐፍ መደርደሪያ ሼልፍ፤ የአየር ማስወጫ እና ሽታ መከላከያ /ኤር ኮንዲሽነር/የመናፈሻ ወንበር፤ አልጋ ድንኳን ፤ የመጸዳጃ ገንዳ፤ ስላይድ ፕሮጀክተር እና 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ ቀረጥ እና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ::

## 5 ምድብ አምስት

5.1 በዚህ ምድብ የተመደቡ ባለመብቶች ከዚህ በታች በቁጥር 5.2 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ከቀረጥ ነጻ ማስገባት ይችላሉ::

5.2 ቁም ሳጥን ፤ አረቢያን መጅሊስ፤ ሶፋ፤ የመጠጥ/የዕቃ ማመላለሻ ጋሪ/ ፤ የጋዝ ምድጃ፤ የጋዝ ስሊንደር ትልቁ፤ የውሃ ማሞቂያ፤ የባኞ ገንዳ፤ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስኪሌት/መሮጫ/፤ የጠረጴዛ ቴኒስ ማጫወቻ ሴት፤ የቤት ውስጥ ፒያኖ፤ ጊታር፤ አልጋ፤ ድሬሲንግ ቴብል፤ የሳሎን ጠረጴዛ ፤ ወንበር፤ እስፕሪንግ፤ ቲቪ፤ ዴክ ፤ ቪ.ሲ.ዲ፤ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር ፤ ላፕ ቶፕ ኮምፒዩተር፤ ፕሪንተር ፤ፍሪጅ፤ ቫክዩም ኪሊነር፤ የጸጉር ካስክ ፤ የጸጉር እስቲም፤ ቲቪ ራክ፤ የአዋቂ ብስክሌት፤ ቪዲዮ ካሜራ፤ የዕቃ ማጠቢያ ማሽን ፤ የሳር ማጨጃ መኪና፤ ጄኔራተር ባለ4 ኪሎዋት ሃንድ ቱል ሴት አነስተኛ፤ ሳታላይት ዲሽ ከነሪሲቨሩ፤ የልብስ ስፌት መኪና ከነዲናሞ፤ የመኪና ጎማ ከነቻርኬው፤ ኮንትሮል ብሬ፤ የመጽሀፍ መደርደሪያ ሼልፍ፤ የአየር ማስወጫ እና ሽታ ማከላከያ/ኤር ኮንዲነሽነር/፤ የመናፈ ወንበር፤ አልጋ፤ ድንኳን፤ የመጸዳጃ ገንዳ፤ ስላይድ ፕሮጀተር እና 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ ቀረጥ እና ታክስ በመክፍል ማስገባት ይችላሉ::

6 <u>ለየምድቦቹ ከቀረጥ እና ታክስ በነጻ ለማስገባት ከተፈቀዱት የኤሌክትሪክ፤ የኤሌክትሪክስ፤ የሳሎን ቤት እና የመኝታ ቤት ዕቃዎች በላይ በትርፍነት የሚመጡ የንግድ መጠን እና ባህሪ የሌላቸው የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ባለው ተቀጽላ 1 መሠረት ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው እንዲገቡ ይደረጋል::</u>

7 በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1.6 ድረስ የተደነገጉት ቢኖሩም ፎቶ ኮፒ ማሽን፤ ቪዲዮ ካሜራ፤ ሞተር ሳይክል፤ ትልቁ የቡና ማሽን፤ ላሚኔተር፤ ባይንደር ሌሎች ተመሳሳይ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያዎች መጠናቸው ከአንድ ያልበለጠ ተገቢው ቀረጥ እና ታክስ ተከፍሎባቸው ሊገቡ ይችላሉ።

8 ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ፎቶ ኮፒ ማሽን/personal Grade desktop photocopy machine/ ሲሆን አማካኝ አካላዊ መለኪያቸው

-ወርዳቸው ከ16.05 ኢንች /40.77 ሴ.ሜ/ ያልበለጠ ።

-ቁመታቸው ከ13.84 ኢንች /35.15 ሴ.ሜ/ ያልበለጠ ።

-ክብደታቸው ከ36.47 ፓውንድ/17.64 ሴ.ሜ/ ያልበለጠ ።

-ስፋታቸው ከ18.77 ኢንች /47.68 ሴ.ሜ/ ያልበለጠ ።

ሲሆን የክብደቱ መጠን ከተገለጸው መለኪያ 10% መብለጥ የለበትም።

# <u>ክፍል ሁለት</u>
# <u>ስለባለመብቶች አመዳደብና ተያያዥ ጉዳዮች</u>

## አንቀጽ 7 የባለመብቶች አመዳደብ

**በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለመብቶች አመዳደብ እንደሚከተለው ይሆናል።**

### 1/ ምድብ አንድ

ሀ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2/4/ የተመለከቱት ዲፕሎማቶች በውጭ አገር በዲፕሎማትነት ሲያገለግሉ ቆይተው ሥራቸውን አጠናቀው ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ሥራቸውን አቋርጠው ወይም ጡረታ በመውጣት የሚመለሱ፤

ለ. በመንግሥት ጥሪ የሚመጡ ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች፤

### 2/ ምድብ ሁለት

ሀ. በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም የልማት ድርጅቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሶስት ዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገሉና የሥራ ጊዜያቸውን ጨርሰው ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት አቋርጠው የሚመለሱ፤

ለ. በውጭ አገር ያፈሩትን ሀብት በአገር ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ የሚመጡና የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው በውጭ አገር ኗሪ ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች እንዲሁም አግባብ ካለው አካል የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኘ ማንኛውም የውጭ ኢንቨስተር፤

ሐ. በተራድኦ ስምምነት መሠረት የሚመጡ የውጭ ዜጎች ፤

መ. ከትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጪ ዜጎች በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ የውጪ ዜጎች፤

ሠ አንድ የትምህርት ዘመንና ከዚያ በላይ የከፍተኛ ትምህርት ሲከታተሉ ቆይተው ተምህርታቸውን አጠናቀው የሚመለሱ፤

ረ. ለከፍተኛ ትምህርት ውጭ አገር ሄደው ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ለምርምር ሥራ በመካከሉ የሚመለሱ ተማሪዎች በዚህ ምድብ ተመድበው ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ ከሚያመጡት ዕቃ ላይ ታሳቢ ሆኖ የሚያዝ መኪናን ሳይጨምር ከምርምር ሥራው ጋር በተያያዘ የሚያስፈልጓቸው ዕቃዎች እየተመዘገቡ እንዲገቡ ይፈቀዳል፤ ለምርምር ሥራው የሚያስፍልጉ ሆነው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(2) ውስጥ ያልታቀፉ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ግን በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ከቀረጥ ነጻ በጊዜያዊነት የሚገቡ ይሆናሉ፡፡

ሰ. አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ በውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፤

ሸ. ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች በግላቸው ተወዳድረው የተቀጠሩና የዲፕሎማቲክ ማዕረግ የሌላቸው ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግለው የሚመለሱ፤

ቀ. በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር የቅጥር የሥራ ውል በማድረግ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ በማያስፈልጋቸው የንግድ ሥራዎች ላይ በመሰማራት የሚመጡ ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች፤

## 3/ ምድብ ሦስት

አንድ ዓመትና በላይ ከአምስት ዓመት በታች ውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፤ ከሦስት ዓመት በታች እስከ አንድ ዓመት ሠርተው የሚመለሱ የቅርንጫፍ መ/ቤቶች ሠራተኞች፤ የዲፕሎማቲክ ማዕረግ የሌላቸው የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ባልደረቦች፤

## 4/ ምድብ አራት

ሶስት ወር እና በላይ ከአንድ ዓመት በታች ውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፤ የቅ/መ/ቤት ሠራተኞች፤ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ባልደረቦች፤ እንዲሁም ለሥራ፤ ለሴሚናር፤ ለትምህርት፤ ለጉብኝት እና ለሕክምና ቆይተው የሚመለሱ፤

## 5/ ምድብ አምስት

ሀ. በትምህርት፤ በመንግስት ሥራ፤ በህክምና፤ በጉብኝት ወይም በሌላ ምክንያት ከሶስት ወር በታች ውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፤

ለ. በውጭ አገር ከቤተሰብ ጋር በጥገኝነት ኖረው የሚመለሱ ዕድሚያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን፤

ሐ. ስደተኞች፤

6/ በአንቀጽ 7(1) (ለ)፤ 2(ለ) እና (2) (ቀ) ከተመለከቱት በስተቀር በማናቸውም ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የሚመጡ ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች ከተመላሽ ኢትዮጵያውያን ምንም ልዩነት ሳይደረግ በውጭ አገር ባላቸው ቆይታ መጠን እንደ ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ተቆጥረው ከምድብ 2 እስከ ምድብ 5 ተመድበው የሚስተናገዱ ይሆናሉ::

**አንቀጽ 8 ስለኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ሠራተኞች**

**በመርከብ ላይ የሚሰሩ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ሠራተኞች፤**

ሀ. ሥራቸውን አጠናቀው ጠቅልለው የሚመለሱት እንደማንኛውም የቅርንጫፍ መ/ቤት ሠራተኞች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ይስተናገዳሉ::

ለ. በየዓመቱ እረፍት እያገኙ በመርከብ ላይ 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገሉት በዚህ መመሪያ በምድብ 2 ተመድበው ሊስተናገዱ ይችላሉ::

**አንቀጽ 9 ለከፍተኛ ትምህርት ሄደው አቋርጠው ስለሚመለሱ ኢትዮጵያውያን**

አንድ የትምህርት ዘመንና ከዚያ በላይ የከፍተኛ ትምህርት ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያት ትምህርታቸውን አቋርጠው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን እንደቆይታቸው መጠን በተመላሽነት ይስተናገዳሉ::

**አንቀጽ 11 ለሥራ ወደ ውጭ ሄደው ስለሚመለሱ ልዑካን**

1/ በምድብ አምስት (5) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያን መንግስት ወይም የአንድ መንግሥት መ/ቤትን በመወከል ከኢትዮጵያ ውጭ ለሥራ ሄደው የሚመለሱ የመምሪያ እና ከዚያ በላይ ኃላፊ የሆኑ የመንግሥት ሠራተኞች ከቀረጥ ነጻ እና ወይም በቀረጥ የሚያስገቧቸው የግል መገልገያ ዕቃዎች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ተቀጽላ ሁለት (2) የተመለከቱት ይሆናሉ::

2/ እነዚህ የልዑካን አባላት በተቀጽላ 2 የተመለከቱትን ዕቃዎች በዚሁ ተቀጽላ መሠረት ካስገቡ በተመሳሳይ ጊዜ ለምድባቸው በተሰጣቸው መብት መሠረት ለማስገባት የሚችሉት ያላስገቡትን ብቻ ነው::

## ክ ፍ ል ሦስት

## ስለማስረጃዎች አቀራረብ

## አንቀጽ 12 ዲፕሎማቶች ስለሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2(4) በትርጓሜ የተመለከቱት ዲፕሎማቶች የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች:-

1. በውጭ አገር በኢትዮጵያ ሚስዮን በዲፕሎማት ደረጃ አገልግለው የሚመለሱ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንኑ የሚገልጽ ደብዳቤ፤

2. ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች በዲፕሎማት ደረጃ የተመደቡ ወይም ራሳቸው ተወዳድረው በዚህ ማዕረግ የተቀጠሩና ያገለገሉ ወይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዕውቅና ባገኙ ተቋማት ተመድበው የሠሩ ካገለገሉበት ድርጅት፤ ከነበሩበት አገር የኢትዮጵያ ሚሲዮን የተሰጠ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ደብዳቤ ይሆናል::

## አንቀጽ 13 በመንግሥት ጥሪ የሚመጡ

በመንግሥት ጥሪ የሚመጡ ተመላሾች ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ወይም ጥሪውን ካደረገው ሚኒስቴር በሚኒስትር ወይም ም/ሚኒስትር የተፈረመ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

## አንቀጽ 14 የቅርንጫፍ መ/ቤት እና ከዲፕሎማት ማዕረግ ውጪ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅት ሠራተኞች፤

የቅርንጫፍ መ/ቤት ሠራተኞችና በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው ሲያገለግሉ ቆይተው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን:-

1. በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አገልግለው የሚመለሱ ከዋናው መሥሪያ ቤታቸው እና ከነበሩበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተጻፈ የመሸኛ ደብዳቤ፤

2. የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ሠራተኛ ግን በማኔጂንግ ዳይሬክተሩ ወይም በማኔጂንግ ዳይሬክተሩ በተወከለ ኃላፊ የተጻፈ ደብዳቤ ባህረኛው መርከብ ላይ የቆየበትን ጊዜ መጠን የሚገልጽ በሠራበት መርከብ አዛዥ የተፈረመበት የባህረኛነት ደብተር /ሲማን ቡክ/ ወደ መርከብ ለሥራ ሲወጣ ያወጣው ፓስፖርትና ቪዛ እንዲሁም ወደ አገር ውስጥ የገባበት ጊዜ ማረጋገጫ ማሟላት አለበት፤

3. ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅት ውስጥ አገልግለው የሚመለሱ ይሰሩበት ከነበረው ዓለም አቀፍ ድርጅት የአገልግሎት ዘመናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ እንዲሁም ከነበሩበት አገር የኢትዮጵያ ሚሲዮን መሸኛ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 15 ተመላሾች

1. ተመላሾች በውጭ አገር የቆዩበትን ጊዜና ጠቅለው ወደ አገራቸው መመለሳቸውን የሚገልጽ የመሸኛ ደብዳቤ ከነበሩበት አገር የኢትዮጵያ ሚስዮን የሚያቀርቡ ሲሆን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ (authenticated) መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው በተጨማሪ ማንኛውም ተመላሽ እንደ የአገሩ እና እንደየኑሮው ሁኔታ፡-

   ሀ. ይሠራ ከነበረበት የሥራ ቦታ መልቀቁን፤

   ለ. ጡረታ የወጣ ከሆነ ጡረታ መውጣቱን፤

   ሐ. ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ የሚያስገቧቸውን ዕቃዎች ዝርዝር ለኢትዮጵያ ሚሲዮን በማቅረብ በሚሲዮኑ ተጣርቶና ተመዝግቦ ከሚሰጠው መሸኛ ጋር የግል መገልገያ ዕቃዎችን ወደ አገር የሚያስገባበትን ሁኔታ የሚያሳውቅ መረጃ የተቀበለ ለመሆኑ የፈረመበትን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

3. ጥገኞች ደግሞ ከኢትዮጵያ ሚሲዮን የመሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. የኢትዮጵያ ሚሲዮን ከሌለበት አገር የሚመጡትን ተመላሾች በተመለከተ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመኖሪያ ፈቃዳቸውን እና የሥራ ውላቸውን ሣያስርዙ የሚመጡትን በማጣራት በፓስፖርታቸው ላይ በተለጠፈው እስቲከር ላይ ተሰርዟል (Void) የሚል ማህተም በማድረግ የሚሰጣቸውን የመሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 16 ስደተኞች

1. የጥገኝነት ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ በስደት ኖረው የሚመለሱ ወይም የጥገኝነት ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ወደ አገራቸው በሊሴ ፓሴ

የሚመለሱ ስደተኞች ከሚኖሩበት አገር ሚሲዮን የተሰጣቸው መሸኛ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ተረጋግጦ ማቅረብ አለባቸው።

2. ከጎረቤት አገሮች አካባቢ በስደተኞች ካምፕ በስደተኝነት ቆይተው በላኪውና በተቀባይ አገር በሚደረግ ስምምነት መሠረት የሚመለሱ ስደተኞች ከደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን የመሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው።

## አንቀጽ 17 ኢንቨስተሮች

1. በውጭ አገር ያፈሩትን ሀብት በአገር ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ የሚመጡ በውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ ሚሲዮን የተጻፈላቸውን በውጭ ነዋሪ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤና ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም አግባብ ካለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ፤ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች ደግሞ የትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ መታወቂያ እና ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም አግባብ ካለው የክልል የኢንቨስትመንት መ/ቤት የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ፤ ለገቢዎች ሚኒስቴር የቀረጥ ነጻ መምሪያ በማቅረብ ከመምሪያው ስለኢንቨስትመንቱ እንቅስቃሴና ተግባራዊ ተሳትፎ የተሰጠ የማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

2. ማንኛውም የውጭ ዜጋ ኢንቨስተር ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም አግባብ ካለው የክልል ኢንቨስትመንት አካል የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ፈቃድና ስለኢንቨስትመንቱ እንቅስቃሴና ተግባራዊ ተሳትፎ ከገቢዎች ሚኒስቴር የቀረጥ ነጻ ማስፈጸሚያ መምሪያ የተሰጠ የማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት።

## አንቀጽ 18 ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች

ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች በዚህ መመሪያ  የተመለከቱትን መብቶች ለመጠቀም፤

1) መንግስት ጥሪ ሳያደርግላቸው የመጡም ቢሆን በሙያና እውቀት ሽግግር በመንግስት መ/ቤቶች የሚያገለግሉ እውቅ ባለሙያዎች አገልግሎት ከሚሰጡበት መ/ቤት የበላይ ሃላፊ ተረጋግጦ የተጻፈ ደብዳቤ የትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ መታወቂያ እና ፓስፖርት፤

2) በኢንቨስትመንት የሚሣተፉት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 የተጠቀሱትን ማስረጃዎችና ፓስፖርት፤

3) በንግድ የሚሣተፉት የትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ መታወቂያ፤ ፓስፖርት፤ የንግድ ፈቃድ እና ስለንግዱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ አግባብ ካለው ግብር ሰብሳቢ አካል የተጻፈ ደብዳቤ፤

4) በእውቀትና በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚመጡት የትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ መታወቂያ፤ ፓስፖርት፤ ከ1 ዓመት ያላነሰ የቅጥር/የሥራ ውል ማስረጃ፤

5) በውጭ አገር ባላቸው ቆይታ መጠን ከዚህ መመሪያ እንደ ተመላሽ ኢትዮጵያዊ የሚቆጠሩት ትውልድ ኢትዮጵያውያን የውጭ ዜጎች የትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ መታወቂያ፤ ፓስፖርት እና በውጭ አገር የኖሩበትን የጊዜ ርዝመት የሚያስረዳ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው::

**አንቀጽ 19 ለትምህርት ሄደው የሚመለሱ**

1) ለከፍተኛ ትምህርት በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ውጭ አገር ተልከው ተምረው የሚመለሱ የትምህርቱን ጊዜና የትምህርቱን የአቻ ግምት የሚገልጽ ከትምህርት ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው::

2) በሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ለከፍተኛ ትምህርት ተልከው ተምረው የሚመጡ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ከኢትዮጵያ ሚሲዮን እና ለትምህርት ከላካቸው አካል በሚጻፍለት መረጃ ላይ በመመሥረት ከትምህርት ሚኒስቴር የሚጻፍ የአቻ ግምቱን ጭምር የሚገልጽ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው::

3) ለከፍተኛ ትምህርት ወደውጭ አገር ሄደው ትምህርታቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት በመካከሉ ለምርምር ሥራ ሚመለሱ ተማሪዎች:-

ሀ. በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የተላኩ ከነበሩበት የትምህርት ተቋም እና ከትምህርት ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤ ወይም ማስረጃ፤

ለ. በሌሎች አካላት የተላኩ ከነበሩበት የትምህርት ተቋም እና ለትምህርት ከላካቸው አካል የተጻፈ ደብዳቤ ወይም ማስረጃ፤

ሐ. በግላቸው የሄዱ ከሆነ ከነበሩበት የትምህርት ተቋም እና የምርምር ሥራውን

ተቀናጅተው ከሚሠሩበት አካል ወይም ድርጅት የተጻፈ ደብዳቤ ወይም ማስረጃ፤ ማቅረብ አለባቸው፡፡

4) በግላቸው በውጭ አገር ተምረው/ሠልጥነው የሚመጡ በትምህርት ላይ የቆዩበትን ጊዜ ጭምር የሚገልጽ ደብዳቤ ከነበሩበት አገር ሚሲዮን እንዲሁም ስለተገኘው የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ ከትምህርት ሚኒስቴር ማቅረብ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 20 በተራድኦ ስምምነት መሠረት የሚመጡ**

በተራድኦ ስምምነት መሠረት የሚመጡ የውጭ ዜጎች ስምምነቱን ከሚያስፈጽመው የኢትዮጵያ መንግስታዊ አካል የትብብር ደብዳቤ፤ የሥራ ፈቃድ እና የቅጥር ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 21 ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የሚመጡ**

ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመጡ የውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ እና የመኖሪያ ፈቃድ ማቅረብ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 22 የመንግሥት ልዑካን እና ለጉብኝት/ለሕክምና ሄደው የሚመለሱ**

መንግሥትን ወይም አንድን የመንግሥት መ/ቤት በመወከል ከኢትዮጵያ ውጭ ለሥራ፤ ለሴሚናር፤ ለአጭር ጊዜ ሥልጠና ወይም ለትምህርት ሄደው የሚመለሱ እንዲሁም ለጉብኝት/ለሕክምና ሄደው የሚመለሱትን ባለሥልጣኑ ፓስፖርታቸውን በማየት የሚያስተናግዳቸው ሆኖ የፓስፖርታቸውን ፎቶ ኮፒ ያቀርባሉ፡፡

## ክ ፍ ል  አ ራ ት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 23 የመገልገያ ዕቃዎች ለማስገባት ስለሚቻልበት ጊዜ**

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7፤ በምድብ 2 በተራ ፊደል ለ፤ ሐ፤ መ፤ ከተመለከቱት በስተቀር ከምድብ 1 እስከ ምድብ 5 የተመለከቱት ሰዎች የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎቻቸውን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚችሉት ወደ አገር ጠቅልለው ከገቡበት ዕለት ጀምሮ በአንድ ዓመት (1) ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡ ሆኖም ዕቃዎቻቸውን አስጭነው መምጣት የሚችሉት በአየር አንድ ጊዜ በመርከብ ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ምድብ 2 በተራ ፊደል (ሐ) የተመለከቱት ወደ አገር የሚገቡ በዚህ አንቀጽ ነዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በ 6 ወራት ወይም በተራድኦ ስምምነቱ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎቻቸውን ለማስገባት ይችላሉ።

3) ኢንቨስተሮች አመቺ በሆነላቸው በማንኛውም ጊዜ ለአንድ ጊዜ ብቻ የግል መገልገያ ዕቃዎቻቸውን ለማስገባት ይችላሉ።

4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(2) የተመለከቱት ወራሾች ወይም ባል/ሚስት ሕጋዊ የወራሽነት ወይም የባል/የሚስት ማስረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ የኢትዮጵያ ሚሲዮን መሸኛ ከሰጠበት ወይም ሚሲዮን ከሌለበት አገር ከሆነ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጻፈበት ቀን ጀምሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተጠቀሰው ጊዜ የሟቾቹን የመገልገያ ዕቃዎች ለማስገባት ይችላሉ። በቤተሰብ ትርጉም የሚታቀፉት በሟቹ ስም ያስገቡትን ዕቃ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ በሟቹ ስም በማውጣት መጠቀም የሚችሉ ሲሆን በስማቸው የንብረት ዝውውር ሲደረግ ግን ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል። በቤተሰብ ትርጉም የማይታቀፉት ግን በሟች ስም ወደ አገር ያስገቡትን ዕቃ ቀረጥና ታክስ ከፍለው ከጉምሩክ ለመረከብ የሚችሉ ይሆናሉ።

5) በዚህ አንቀጽ በተመለከቱት ጊዜዎች ውስጥ የግል መገልገያ ዕቃዎቻቸውን ከቀረጥ እና ታክስ በነጻ ለማስገባት ሳይችሉ ጊዜው ካለፈ በተከታይ 3 ወራቶች ውስጥ ቀረጥና ታክስ ከፍለው ለማስገባት ወይም በጉምሩክ ሕግ መሠረት ወደመጣበት አገር እንዲመለሱ ለማድረግ ይችላሉ።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ባለመብቱ ወደ አገር ከተመለሰበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄ ካቀረበ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያውን በቀረጥ እና በታክስ ክፍያ ማስገባት ይችላል።

<u>አንቀጽ 24 የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ለሁለተኛ ጊዜ ለማስገባት ስለሚቻልበት ሁኔታ</u>

1) በዚህ መመሪያ መሠረት ወደ አገር ሲመለሱ ወይም ሲገቡ የግል አውቶሞቢልም ሆነ ሌሎች የግል መገልገያዎችነ ከቀረጥ እና/ወይም በቀረጥ ያስገቡ ቢሆንም በምድብ

2 በተራ ፊደል (ሐ) እና (መ) ከተመለከቱት እንዲሁም በተመላሽነት እና በስደተኛነት ለ2ኛ ጊዜ ከሚመጡት በስተቀር ከምድብ 1 እስከ ምድብ 5 ያሉት፤

ሀ. ወደ አገር ከተመለሱበት ጊዜ ጀምሮ ከ10 ዓመት በኋላ ወደ ውጪ የመሄድ ዕድል ቢያጋጥማቸውና የቆይታ ጊዜያቸው በየምድቡ የተመለከተውን የሚያሟላ ከሆነ ለሁለተኛ ጊዜ በየምድባቸው የሚፈቀደውን የግል አውቶሞቢል፤

ለ. ወደ አገር ከተመለሱ በኋላ ከ5 ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች ከቆዩ በኋላ ወደ ውጭ አገር ከሄዱ እንደቆይታ ጊዜያቸውና እንደ ምድባቸው ከግል አውቶሞቢል በስተቀር ለሁለተኛ ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የግል መገልገያ ዕቃዎች
ለማስገባት ይችላሉ::

2) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በ «ሀ» እና በ«ለ» የተጠቀሰው ጊዜ ከመሟላቱ በፊት ወደ ውጭ የመሄድ እድል ያጋጠመው ሰው ቀደም ብሎ በተጠቀመበት ዕድል ከቀረጥ ነጻ ያስገባቸውን እቃዎች ቀረጥና ታክስ ከፍሎ የሄደ እንደሆነ ለሁለተኛ ጊዜ በምድቡ የሚፈቀድለትን የግል መገልገያ ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት ይችላል:: ቀረጥና ታክሱን ሣይከፍል የሄደ እንደሆነ ግን ለሁለተኛ ጊዜ በምድቡ የሚፈቀድለትን በቀረጥና ታክስ ክፍያ ለማስገባት ይችላል::

3) የመንግስት ወይም የመንግስት መ/ቤት ለዑካን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) የተመለከተው ቢኖርም 5 ዓመት ከመሙላቱ በፊት ወደ ውጭ በሚያደርጓቸው የተልእኮ ጉዞዎች ቀደም ሲል ያላስገቧቸውን የግል መገልገያ ዕቃዎች ለማስገባት ይችላሉ::

4) በምድብ 2 በተራ ፊደል (ሐ) የተመለከቱት በሌላ የተራድኦ ስምምነት መሠረት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ሲያሟሉ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎቻቸውን ሊያስገቡ ይችላሉ::

## አንቀጽ 25 የመብት አጠቃቀም

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ

መሠረት ከቀረጥ ነጻ የገቡ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ባለሥልጣን ለማውጣት፤ ለመረከብ የሚችለው የቀረጥ ነጻ ባለመብቱ ብቻ ነው፡፡

2) በዚህ መመሪያ የቀረጥ ነጻ መብት የተሰጠው ማናቸውም ሰው ከቀረጥ ነጻ ያስገባቸውን የግል አውቶሞቢልም ሆነ ሌሎች የግል መገልገያ ዕቃዎች ከራሱና ከቤተሰቡ የግል መገልገያነት ውጭ በሌላ ጥቅም ወይም አገልግሎት ላይ ማዋል በሕግ የተከለከለ በመሆኑ አግባብ ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመጣስ በሌላ ጥቅም ወይም አገልግሎት ላይ አውሎ የተገኘ እንደሆነ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989 (እንደተሻሻለ) አግባብ ያለው ድንጋጌ መሠረት የሚቀጣ እና እርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል፡፡
3) በዚህ መመሪያ የቀረጥ ነጻ መብት ተጠቃሚ የሆነ ማናቸውም ሰው ከቀረጥ ነጻ ያስገባቸውን አውቶሞቢልም ሆነ ሌላ የግል መገልገያ ዕቃ ከቤተሰብ ውጭ ስሆነ ሰው በውክልና ወይም በማናቸውም ሌላ ሽፋን በመጠቀም በሌላ ሰው ጥቅም ግልጋሎት እንዲውል ማድረግ አይችልም፡፡

4) በቀረጥ ነጻ መብት ተጠቅሞ አውቶሞቢልና የግል መገልገያ ዕቃ ወደ አገር ያስገባ ባለ ልዩ መብት ሲሞት የትዳር ጓደኛው እና በዚህ መመሪያ ለቤተሰብ በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈኑ ወራሾቹ በሟቹ ስም በአውቶሞቢሉና በግል መገልገያ ዕቃዎቹ የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 26 ስለቁጥጥር**

በዚህ መመሪያ መሠረት የተፈቀዱት መብቶች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉና ሕገ-ወጥ አጠቃቀምን ለመቆጣጠር፡-

1. ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ መሠረት በመብቱ የተጠቀሙትን ሰዎች ዝርዝር መዝገቦ ያስቀምጣል፤ ይቆጣጠራል፤ በሚያካሄደው ቁጥጥር መሠረትም አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤ በተጨማሪም ብዛ ቸው በዝርዝሩ ውስጥ በመጠን ያልተጠቀሱ የግል መገልገያ ዕቃዎች ለንግድ በሚውል መጠን ያለመምጣታቸውን ይቆጣጠራል፡፡

2. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፤ የትምህርት ሚኒስቴር፤ የደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን፤አግባብ ያላቸው የኢንቨስትመንት አካላት፤ በውጭ አገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና አግባብ ያላቸው አካላት አንድ ግለሰብ አንድ ጊዜ መብት በሚያሰጠው ጉዳይ ተደጋጋሚ ደብዳቤ እንዳይሰጠው መቆጣጠር ይኖርባቸዋል፡፡

3. የፌዴራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የክልል ኢንቨስትመንት አካላት የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሠረዘ ጊዜ ባለሥልጣኑን ማሳወቅ አለባቸው፡፡

4. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን የትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ መታወቂያ ካርድ ከተሠረዘ ወይም በተገቢው ጊዜ ውስጥ ካልታደሰ ይህንኑ በተመለከተ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/94 በደንቡና በመመሪያው መሠረት አስፈላጊው እርምጃ እዲወሰድ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ የሚኖርባቸው ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 27 የአፈጻጸም መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ባለስልጣኑ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በሚረዱ ጉዳዮች ላይ የአፈጻጸም መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 28 ህጋዊ ተጠያቂነት

ይህንን መመሪያ የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 29 ስለመሸጋገሪ ድንጋጌና ስለመሻር

1. ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን ጀምሮ በዚህ መመሪያ ባለመብቶች ዲክላራሲዮን በሚሞላላቸው ወይም ቀደም ብሎ የተሞላላቸው ቢሆንም ለጉምሩክ ያልቀረቡና ተቀባይነት ያላገኙ የግል አውቶሞቢል፤ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን በፊት ዲክላራሲዮን የተሞላላቸው እና በጉምሩክ ተቀባይነት ያገኙ አፈጻጸማቸው ቀደም ሲል በነበሩት መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

2. በዚህ መመሪያ መሠረት የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን የማስገባት መብት ከሕዳር ወር 1994 ዓ.ም. በፊት የማምረት ሥራ ውስጥ የገቡ ኢንቨስተሮችን አይመለከትም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በምድብ 3 ያሉ የቅርንጫፍ መ/ቤት ሠራተኞች እና የዲፕሎማቲክ ማዕረግ የሌላቸው የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ባልደረቦች የሚያስገቧቸው የግል አውቶሞቢሎች ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን በፊት የተጫኑ ከሆነ በቀድሞው መመሪያ መሠረት እንዲገቡ የሚደረግ ሲሆን ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን በኋላ የሚጫኑት ደግሞ በዚህ መመሪያ መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

4. ከዚህ መመሪያ መውጣት በፊት ሲሠራባቸው የነበሩ መመሪያዎች ሁሉ በዚህ መመሪያ ተተክተው ተሽረዋል፡፡ ሆኖም ቀደም ሲል በእነዚህ መመሪያዎች መሠረት ከቀረጥ ነጻ እና በቀረጥ የገቡ ዕቃዎች በዚህ መመሪያ መሠረት እንደገቡ ተቆጥሮ የዚህ መመሪያ አንቀጾች እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆኑባቸውል፡፡

## አንቀጽ 30 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

1) ይህ መመሪያ ከመስከረም 5 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ከፀናበት ዕለት አስቀድሞ ወደ አገር ለመግባት በተጫኑ እና በመጓጓዝ ላይ በሚገኙ የግል አውቶሞቢሎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ምድብ 1 እና 2

ሶስት ዓመትና ከዚያ በላይ በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም የልማት ድርጅቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ውስጥ ያገለገሉ፤ በውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ኢንቨስተሮች፤ በተራድኦ ስምምነት የሚመጡ የውጭ ዜጎች፤ የአንድ ትምህርት ዘመንና ከዚያ በላይ የከፍተኛ ትምህርት ሲከታተሉ ቆይተው ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመለሱ፤ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ በውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፤ ከእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር በቁጥር/ በሥራ ውል በማድረግና የኢንቨስትመንት ፈቃድ በሚያስፈልጋቸው የንግድ ሥራዎች ላይ በመሠማራት የሚመጡ፤

<u>**ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው የሚገቡ**</u>

1) ስላይድ ፕሮጀክተር
2) 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ
3) ከ29 ኢንች በላይ የሆነ ቴሌቪዥን በልዩነቱ ላይ ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል፡፡

<u>**ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ**</u>

1) ቁምሳጥን
2) ኮንትሮል ብፌ
3) አልጋ
4) ድሬሲንግ ቴብል
5) የሳሎን ጠረጴዛ
6) ወንበር
7) አረቢያ መጅሊስ
8) ሶፋ ሌዘር/ሶፋ የጨርቅ
9) ስፕሪንግ ፍራሽ
10) የመጽሐፍ መደርደሪያ ሽልፍ
11) የመጠጥ/ዕቃ/ማመላለሻ ጋሪ
12) አየር ማስወጫ ያና ሽጻ መከላከያ /ፋን/
13) ወንበር የመናፈሻ
14) አልጋ የመናፈሻ
15) ቲቪ ራክ
16) ምንጣፍ ሲንቴቲክ 3X4Mt

17) ምንጣፍ ጆንያስራ 3X4Mt
18) የጋዝ ምድጃ ባለ መጣጃ
    የጋዝ ምድጃ ባለ 4 መጣጃ
    የጋዝ ምድጃ ባለ 5 መጣጃ
19) የወጥ ቤት ዕቃ ማጠቢያ ሲንክ
20) የአትክልት/የምግብ/ መፍጫ ፕሮሰሰር
21) የጋዝ ሲሊንደር ትልቁ
22) ኦቭን
23) የውኃ ማሞቂ ግድግዳ ላይ ተለጣፊ
24) የፀጉር መታጠቢያ ገንዳ
25) የባኞ ገንዳ
26) የመጸዳጃ መቀመጫ ገንዳ
27) የአዋቂ ብስክሌት
28) በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መፍጫ
29) በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስክሌት
30) የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻ ካሴት
31) ፒያኖ ባለእግር ለቤት ውስጥ አገልግሎት
32) የሙዚቃ ኪ ቦርድ መጫወቻ
33) ጊታር
34) ቪዲዮ ካሜራ መካከለኛ
    ቪዲዮ ካሜራ NVM9500 cm
    ቪዲዮ ካሜራ ትንሹ
35) ቲቪ ከዴክ ጋር 21 ኢንች
36) ደብል ዴክ
37) ዴክ ኖርማል
    ቪሲዲ
    ዲቪዲ
38) ዴስክቶፕ ኮምፒዩተር
39) ላፕቶፕ ኮምፒዩተር
40) ፕሪንተር ኖርማል
41) ፍሪጅ CFC
    Based
42) የዕቃ ማጠቢያ ማሽን

43) የልብስ ማጠቢያ ማሽን
44) ቫኪዩም ክሊነር
45) የቴፕ እስፒከር
46) የመኪና ቴፕ ከነስፒከር
47) ፋክስ
48) የፀጉር ካስክ
49) የፀጉር እስቲም
50) 4 inone fax/printer,copier
51) ስካነር
52) የተለያዩ ድሪል 500 ዋት
53) ቲቪ
    ባለ 14 ኢንች
    ባለ 20 ኢንች
    ባለ 21 ኢንች
    ባለ 25 ኢንች
    ባለ 29 ኢንች
54) ሲዲ ማጫወቻ
    ባለ 1 ባለ ሁለት ካሴት ማጫወቻ
    ባለ 3 ባለ ሁለት ካሴት ማጫወቻ
    ባለ 5 ባለ ሁለት ካሴት ማጫወቻ
    ባለ 9 ባለ ሁለት ካሴት ማጫወቻ
55) የግል አውቶሞቢል
56) የሳር ማጨጃ አነስተኛ መኪና
57) ጀኔሬተር ባለ 4 ኪሎ ዋት
58) ሐንድ ቲልስ ሴት አነስተኛ
59) ሳተላይት ዲሽ ከነሪሲቨርና
    አልአንቢ
    ዲሽ ሻጎን
    ሀቢቨር
    ኤልኤንቢ
60) የልብስ ስፌት መኪና ከነዲናሞ
61) የመኪና ጎማ ከነቸርኬው
62) ለግል መገልገያ ለሆነ የመኪና መለዋወጫ

አገር ውስጥ አለመኖሩ ማረጋገጫ ከብቸኛ
አስመጪ ካምፓኒው የተሰጠበት እና
የባለቤትነት ማረጋገጫ የሚቀርብበት

<u>ምድብ 3</u>

የአንድ ዓመትና በላይ ከአምስት ዓመት በታች በውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፤ ከሦስት ዓመት በታች እስከ አንድ ዓመት ሠርተው የሚመለሱ የቅርንጫፍ መ/ቤቶች ሠራተኞች፤ የዲፕሎማቲክ ማዕረግ የሌላቸው የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ባልደረቦች፤

<u>ቀረጥና ታክስ በመክፈል</u>

1. ኮንትሮል ብሬ
2. የመጽሐፍ መደርደሪያ ሼልፍ
3. አየር ማስወጫና ሽታ መከላከያ /ፋና/
4. ወንበር የመናፈሻ
5. አልጋ የመናፈሻ
6. ድንኳን የመናፈሻ
7. የመጸዳጃ መቀመጫ ገንዳ
8. የሳር ማጨጃ አነስተኛ መኪና
9. ጀኔሬተር ባለ 4 ኪሎዋት
10. ሐንድ ቱልስ ሴት አነስተኛ
11. የመኪና ጎማ ከነቸርኬው
12. ስላይድ ፕሮጀክተር
13. 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ

<u>ከቀረጥና ታክስ ነጻ</u>

1. ቁምሳጥን
2. አልጋ
3. ድሬሲንግ ቴብል
4. የሳሎን ጠረጴዛ
5. ወንበር
6. አረቢያ መጅሊስ

7. ሶፋ ሌዘር
   ሶፋ የጨርቅ
8. ስፕሪንግ ፍራሽ
9. በመጠጥ/ዕቃ/ማመላለሻ ጋር
10. ቲቪ ራክ
11. ምንጣፍ ሴንቴቲክ 3x4mt
12. ምንጣፍ ጆንያ ስራ 3x4mt
13. የጋዝ ምድጃ ባለ 2 መጣጃ
14. የጋዝ ምድጃ ባለ 4 መጣጃ
15. የጋዝ ምድጃ ባለ 5 መጣጃ
16. የወጥ ቤት ዕቃ ማጠቢያ ሲንክ
17. የአትክልት/የምግብ/መፍጫ ፕሮሰሰር
18. የጋዝ ስሊንደር ትልቁ
19. ኦቨን
20. የውሃ ማሞቂያ ግድግዳ ላይ ተለጣፊ
21. የፀጉር መታጠቢያ ገንዳ
22. የባኞ ገንዳ
23. የአዋቂ ብስክሌት
24. በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መሮጫ
25. በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስክሌት
26. የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻ በሴት
27. ፒያኖ ባለእግር ለቤት ውስጥ አገልግሎት
28. የሙዚቃ ኪ ቦርድ መጫወቻ
29. ጊታር
30. ቪዲዮ ካሜራ መካከለኛ
31. ቪዲዮ ካሜራ NVM9500 cm
32. ቪዲዮ ካሜራ ትንሹ
33. ቲቪ ኮዳክ ጋር 21 ኢንች
34. ደብል ዴክ
35. ዲክ ኖርማል
36. ቪሲዲ
37. ዲቪዲ
38. ዴስክቶፕ ኮምፒዩተር

39. ላፕቶፕ ኮምፒዩተር
40. ፕሪንተር ኖርማል
41. ፍሪጅ
42. የዕቃ ማጠቢያ ማሽን
43. የልብስ ማጠቢያ ማሽን
44. ቫኪዩም ክሊነር
45. የቴፕ እስፒከር
46. በመኪና ቴፕ ከነስፒከር
47. ፋክስ
48. የፀጉር ካስክ
49. የፀጉር እስቲም
50. 4 in one fax, printer, copier and scanner
51. ስካነር
52. የተለያዩ ድሪል ጨዋታ
53. ቲቪ
54. ባለ 14 ኢንች
55. ባለ 20 ኢንች
56. ባለ 21 ኢንች
57. ባለ 25 ኢንች
58. ባለ 29 ኢንች
59. ሲዲ መጫወቻ
60. ባለ 1 ባለሁለት ካሴት ማጫወቻ
61. ባለ 3 ባለሁለት ካሴት ማጫወቻ
62. ባለ 5 ባለሁለት ካሴት ማጫወቻ
63. ባለ 9 ባለሁለት ካሴት ማጫወቻ
64. ሳተላይት ዲሽ ከነሪሲቨሩ
65. ኤል ኤንቢ
66. ዲሽ ሣህን
67. ሪሲቨር
68. ኤል ኤንቢ
69. የልብስ ስፌት መኪና ከነዲናሞ
70. ለግል መገልገያ ለሆነ የመኪና መለዋወጫ አገር ውስጥ አለመኖሩ ማረጋገጫ የተሰጠበት እና የባለቤትነት ማረጋገጫ የሚቀርብበት፡፡

## ምድብ 4/አራት/

(ከሶስት ወር በላይ እና ከአንድ ዓመት በታች ቆይታ የሚመለሱ ተመላሾች፤ የቅርንጫፍ መ/ቤቶች ሠራተኞች፤ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ባልደረቦች፤ እንዲሁም ለስራ፤ ለሴሚናር፤ ለትምህርት፤ ለጉብኝት እና ለህክምና ቆይተው የሚመለሱ)

<u>ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው የሚገቡ</u>

1. ቁምሳጥን
2. አረቢያን መጅሊስ
3. የመጠጥ/የዕቃ ማመላለሻ ጋሪ
4. የጋዝ ምድጃ
5. የጋዝ ስሊንደር ትልቁ
6. የውሃ ማሞቂያ
7. የባኞ ገንዳ
8. በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስክሌት/መሮጫ
9. ሶፋ
10. የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻ ሴት
11. ፒያኖ የቤት ውስጥ አገልግሎት
12. ጊታር
13. ቪዲዮ ካሜራ
14. የዕቃ ማጠቢያ ማሽን
15. የሳር ማጨጃ መኪና
16. ጄኔራተር ባለ 4 ኪሎዋት
17. ሃንድ ቱል ሴት አነስተኛ
18. ሳተላይት ዲሽ ከነሪሲቨሩ
19. የልብስ ስፌት መኪና ከነዲናሞው
20. የመኪና ጎማ ከነቸርኬው
21. ኮንትሮል በፌ
22. የመጽሀፍ መደርደሪያ ሼልፍ
23. የአየር ማስወጫ እና ሽታ መከላከያ/ኤርኮንዲሽነር/
24. የመናፈሻ ወንበር አልጋ ድንኳን
25. የመጸዳጃ ገንዳ
26. ስላይድ ፕሮጀክተር

27. 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ

## ከቀረጥና ታክስ ነፃ

1. አልጋ
2. ድሬሲንግ ቴብል
3. የሳሎን ጠረጴዛ
4. ወንበር
5. እስፕሪንግ ፍራሽ
6. ቲቪ
7. ዴክ
8. ቪሲዲ
9. ዲቪዲ
10. ዴስክቶፕ ኮምፒዩተር
11. ላፕቶፕ ኮምፒዩተር
12. ፕሪንተር
13. ፍሪጅ
14. ቫኪዩም ክሊነር
15. የፀጉር ካስክ
16. የፀጉር እስቲም
17. ቲቪ ራክ
18. የአዋቂ ብስክሌት
19. ቲቪ ራክ
20. ምንጣፍ ሴንቴቲክ 3x4 ሜትር
    (ምንጣፍ ጆንያ ስራ3x4 ሜትር)
21. የወጥ ቤት ዕቃ ማጠቢያ ሲንክ
22. የአትክልት /የምግብ/ መፍጫ ፕሮሰሰር
23. ኦቭን
24. የፀጉር መታጠቢያ ገንዳ
25. የሙዚቃ ኪቦርድ
26. የቴፕ እስፒከር
27. የመኪና ቴፕ ከነስከፒከሩ
28. ፋክስ

29. 4 in one fax, printer, copier and scanner
30. ስካነር
31. የተለያዩ ድሪል 500 ዋት
32. ሲ.ዲ. መጫወቻ (ከ1-9 ካሴት ማጫወቻ)

<u>ምድብ 5(ከ3 ወር በታች ውጭ አገር በትምህርት፤ በመንግስት ሥራ፤በህክምና በጉብኝት፤ በስደት እንዲሁም በጥገኝነት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች) ቆይተው የሚመለሱ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው የሚገቡ</u>

1. ቁምሣጥን
2. አረቢያን መጅሊስ
3. የመጠጥ/የዕቃ ማመላለሻ ጋር
4. የጋዝ ምድጃ
5. የጋዝ ስሊንደር ትልቁ
6. የውሃ ማሞቂያ
7. የባኞ ገንዳ
8. በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስክሌት/መሮጫ
9. ሶፋ
10. የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻ ሴት
11. ፒያኖ የቤት ውስጥ አገልግሎት
12. ጊታር
13. ቪዲዮ ካሜራ
14. የዕቃ ማጠቢያ ማሽን
15. የሳር ማጨጃ መኪና
16. ጄኔሬተር ባለ 4 ኪሎዋት
17. ሃንድ ቱል ሴት አነስተኛ
18. ሳተላይት ዲሽ ከነሪሲቨሩ
19. የልብስ ስፌት መኪና ከነዲናሞው
20. የመኪና ጎማ ከነቸርኬው
21. ኮንትሮል ብሬ
22. የመጽሀፍ መደርደሪያ ሼልፍ
23. የአየር ማስወጫ እና ሽታ መከላከያ/ኤርኮንዲሽነር/
24. የመናፈሻ ወንበር አልጋ ድንኳን
25. የመጸዳጃ ገንዳ
26. ስላይድ ፕሮጀክተር

27. ሰው የሚይዝ ጆልባ
28. አልጋ
29. ድሬሲንግ ቴብል
30. የሳሎን ጠረጴዛ
31. ወንበር
32. እስፕሪንግ ፍራሽ
33. ቲቪ
34. ዴክ
35. ቪሲዲ
36. ዲቪዲ
37. ዴስክቶፕ ኮምፒዩተር
38. ላፕቶፕ
39. ፕሪንተር
40. ፍሪጅ
41. ቫኪዩም ክሊነር
42. የፀጉር ካስክ
43. የፀጉር እስቲም
44. ቲቪራክ

## <u>ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች</u>

1. ምንጣፍ ሲንቴቲክ 3x4 ሜትር
2. ምንጣፍ ጆንያ ስራ 3x4 ሜትር
3. የወጥ ቤት ዕቃ ማጠቢያ ሲንክ
4. የአትክልት/የምግብ/ መፍጫ ፕሮሰሰር
5. ኦቭን
6. የፀጉር መታጠቢያ ገንዳ
7. የሙዚቃ ኪቦርድ
8. የቴፕ እስፒከር
9. የመኪና ቴፕ ከነስፒከሩ
10. ፋክስ
11. 4 in one fax printer, copier and scanner
12. ስካነር
13. የተለያዩ ድሪል 500 ዋት
14. ማጫወቻ(ከ1-9 ካሴት ማጫወቻ)